የ29ኛዓመት ቁጥር 193፣
አሶሳ ህዳር 7/ 2015
ዓ.ም

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
# ልሣነ ሕግ-ጋዜጣ
# LISAN HIG GAZETA
## Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State

ፖ.ሳ.ቁጥር፣293
ያንዱ ዋጋ‹-----

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት**

**ጠባቂነት የወጣ አዋጅ፣**

---

## አዋጅ ቁጥር 193/2015 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዉሃ ሥራዎች እና ኮንስተራክሽን ድርጅቶች እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 149/2009 ዓ.ም ለመሻር የወጣ አዋጅ፣

የክልሉ ሕዝብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የሃብት ብክነትን ለማስቀረት በስራ ላይ የነበረዉን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዉሃ ሥራዎች እና ኮንስተራክሽን ድርጅቶች እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 149/2009 ዓ.ም መሻር በማስፈለጉ፤

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ ቁጥር 3.1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### አንቀጽ 1
### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ **"የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዉሃ ሥራዎች እና ኮንስተራክሽን ድርጅቶች እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 149/2009 ዓ.ም ለመሻር የወጣ አዋጅ ቁጥር 190/2015 ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላላል፡፡

## አንቀጽ 2

## ስለመሻር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዉሃ ሥራዎች እና ኮንስተራክሽን ድርጅቶች እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 149/2009 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

## አንቀጽ 3

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዉሃ ሥራዎች እና ኮንስተራክሽን ድርጅቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 149/2009 ዓ.ም ድርጅት ዉስጥ ሲሰሩ የነበሩ ሠራተኞች፣ የድርጅቱ ሃብት ንብረት፣አጠቃለይ ፕሮጅቸቶች እንዲሁም የድርጅቱ መብትና ግዴታዎች በደንብ ቁጥር 155/2014 ዓ.ም ወደ ተቋቋመዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ቤጉ ዲቨሎፐመነት ግሩፕ ተሸጋግሯል፡፡

## አንቀጽ 4

## አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት ጊዜ ህዳር 7/2015 ዓ.ም.ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አሶሳ፣

ህዳር 7 ቀን 2015 ዓ.ም

አሻደሊ ሃሰን አልአጀብ

የቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት